አፍሪካ ቲቪ

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

13

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ

(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ")

# سُورَةُ العَلَقِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

ٱقۡرَأۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلَّذِي خَلَقَ ١ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِنۡ عَلَقٍ ٢ ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ٤
عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ٥ كَلَّآ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَيَطۡغَىٰٓ ٦ أَن رَّءَاهُ ٱسۡتَغۡنَىٰٓ ٧ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجۡعَىٰٓ ٨
أَرَءَيۡتَ ٱلَّذِي يَنۡهَىٰ ٩ عَبۡدًا إِذَا صَلَّىٰٓ ١٠ أَرَءَيۡتَ إِن كَانَ عَلَى ٱلۡهُدَىٰٓ ١١ أَوۡ أَمَرَ بِٱلتَّقۡوَىٰٓ ١٢ أَرَءَيۡتَ
إِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰٓ ١٣ أَلَمۡ يَعۡلَم بِأَنَّ ٱللَّهَ يَرَىٰ ١٤ كَلَّا لَئِن لَّمۡ يَنتَهِ لَنَسۡفَعَۢا بِٱلنَّاصِيَةِ ١٥ نَاصِيَةٖ كَٰذِبَةٍ
خَاطِئَةٖ ١٦ فَلۡيَدۡعُ نَادِيَهُۥ ١٧ سَنَدۡعُ ٱلزَّبَانِيَةَ ١٨ كَلَّا لَا تُطِعۡهُ وَٱسۡجُدۡۤ وَٱقۡتَرِب ۩ ١٩



AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

# ሱረቱ አል-ዐለቅ

- (የረጋ ደም ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡
- የአናቅፅ ብዛት (19) ናቸው፡፡

## ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-

- የሰው ልጅ ምሉዕነት የሚረጋገጠው በዕውቀት እንዲሁም ጌታውን እንዲገዛና ለእርሱ ፍጹም ታዛዥ ለመሆን የሚያበቃውን ራዕይ የተከተለ እንደሆነ እና በአንፃሩ ደግሞ ይህንን ከተፃረረ ለጉድለት እና ለውድቀት የሚዳረግ መሆኑን
የሚያብራራ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ይህ ምዕራፍ ሱረቱ ኢቅራእ፤ ሱረቱ አል ኢቅራእ ቢስሚረቢከ፤ ሱረቱ አል ኢቅራእ ወል ዐለቅ፤ ሱረቱ
- አልቀለም በመባልም ይታወቃል፡፡
- ይህ ምዕራፍ ከቁርኣኑ ምእራፎች ሁሉ በመጀመሪያ የወረደ ቢሆንም ማንበብና መፃፍ አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል፡፡
- ያኔ ነብያችን ሰለላሁ አሌይሂ ወሰለም እድሜያቸው ወደ 40 እየተቃረበ ሲመጣ፤ ገና ሳይላኩ ነብይ ሳይሆኑ መህበረሰቡ ከሚያደርጉት ነገር ከሠው መነጠልን በተለያዩ ጊዜያት እየወደዱት መጡ። 'ጋሩ ሒራ' ተብሎ የሚጠራ ተራራ ላይ ሆነው ሰማይና ምድርን ተራራን እያስተዋሉ እነዚህን የፈጠረ ብቸኛ አምላክ አለ እያሉ ይማጸኑ ይጸልዩ ነበር (ሂራዕ ማለት ከመካ በሰሜን ምዕራብ የሚገኝ ተራራ ነው፡፡) በዚሁ ሁኔታ
- ብቻቸውን እያሉ ከእለታት አንድ ቀን ጂብሪል
- አሌሂ ሰላም ድንገት መጣባቸው፤ ከዚያም ኢቅረዕ
- ወይም አንብብ በማለት አዘዛቸው፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) አንተ መልዕክተኛ ሆይ! ጌታህ የሚያስተላልፍልህን ራዕይ ፍጡራንን በፈጠረው በጌታህ ስም በመጀመር አንብብ።
- (2) ከፍትወት ጠብታነት ቀጥሎ ከረጋ ቁራጭ ደም የሰውን ልጅ በፈጠረው ጌታ ስም።
- (3) አንተ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ የሚያስተላልፍልህን ራዕይ አንብብ። ቸሩ ጌታህም በቸርነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት እጅግ
  ለጋስና መልካምን የሚውል ነው።



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

- (4) ያ የእጅ ፅሁፍንና በብዕር መፃፍን ያስተማረ፤
- (5) የሰው ልጅን የማያውቀውን ያሳወቀ፣ (ያ በብዕር ለሰው ልጅ ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ጌታ ነው፡፡)